# ጥቁሩ ጉድጓድ

በኮስሞስ-2000, March 2010

ክብ መሳይ! ቁልጭ ያለች!
በእርግብግቢት የታጀበች
ወለል! ከብለል ባይ!
እንደ ፀሐይ!
የብርሐንን ጉልበት ጠልፋ የምታሳይ
ዓይን! ቁሳካላዊ ጉዳይ
ከሕሊና አዋህዳ ፈንጣቂ ራዕይ!!

የጉድጓዱ ውስጥ ፅልመቱ
ዚቅ ቢሆን ነው ጥልቀቱ::
የገባ ሁሉ አይመለስ
አንዳች ነገር እርኩስ መንፈስ
ውጦ አስቀሪ እንጦሪጦስ::
ገብቶ ገብቶ ተጠቅጥቆ
ወርደ-ጠባብ ግን እጅግ ከብዶ
አቤት ጉሮሮ! አዋዋጡ!
ምልዓተ ሕዝብን እያስማጡ
ዓለማችን አጠቃሎ መሰልቀጡ::

ጉድጓዱማ ከሩቅ ስቦ
ጎተት አርጎ አስግብቶ
አንጥሮ የሚያስወጣ መች ተገኝቶ
ውስጥ አካሉን ማንስ ዐይቶ
ማንስ ተመራምሮ ከውስጥ ጠልቆ
ከእምብርቱ
ምን እንዳለ ምንስ ታውቆ?
ውስጡ በጨለማ ተጥለቅልቆ::

ሰተት ብሎ የገባውም ተንደርድሮ

ተሸቀዳድሞ     ተስገብግቦ
እስቲመለስ     ተጠብቆ
ግን ሽምጥ ወርዶ     እጅግ ጠልቆ
ተመሳስሎ! ተጣብቆ     ተጨፍልቆ!
እልም ይላል     እጅግ ደቆ
ምንነቱን     አጥቶ!
ሙሉ በሙሉ ተውጦ!     ተለውጦ!
ላይመለስ ዘግጦ!     በዛው ቀልጦ!

ለስበቱ ጉልበት     ተቃራኒ
አልገኝ ብሎ     የላቀ ተወዳዳሪ
እጥፍ አርጎ     ተምዘግዛጊ!
ተፃራሪ!
በውስጣዊ     የግፊት ኃይል ተወርዋሪ!
ባይኖር ነዋ     አስፈንጣሪ!
ተስፈንጣሪ!

መልዕክት ልከን     መልስ ካልመጣ
ምኑ ታውቆ     ስለዚያ ቦታ
የጨበጠው ቁም ነገሩ     በይዞታ
ሃቅን ማን ይያዛት?     እንዴት ወጥታ?
ካላወቅናት     በልኬታ
አትሆንማ
የዕውቀት አካል     የዕውነታ::

እነሆ ጊዜ!     እነሆ ቦታ!
የመዳረሻችን     ዕውነታ
እጅግ በማዝገም     ቀርቦ ለውህደት
ባዶ እስከሚሆን     እርቀት
ተሳስሮ     በሥርዬት
ለመራመድ     በዕድገት
በአንድነት

የጉድጓዱ ማህፀንማ    እጅግ ሰፍቶ
አጎልብቶ!
የዕውቀት መለኪያ    መሆኑ ቀርቶ
ከአፅናፍ እስከ አፅናፍ    ተጠልቶ
ከጥፋቱ በቀር    ምን ተገኝቶ?
ሞራል ሰብሮ!    ራዕይ አጥፍቶ!
ወኔን ሰልቦ!    አስፈራርቶ!
ያኖረዋል አደንዝዞ!    አስተኝቶ
እርስ በርሱ    አበላልቶ!
አፋጅቶ!

ግን ጠቢቡ ሰለሞን    አሰላስሎ
አውርዶ!    አውጥቶ!
"ጊዜ ለኩሉ" ብሎ    ለእኛ ሰጥቶ
ቀጣዩ ትውልድ
ይህ ሃቅ መሆኑን    ተረድቶ
በጊዜ ተምሮ    ተመራምሮ!
በመልካም ፈቃድ    ተነሳስቶ
ድንቁርናን    አጥፍቶ
ሁለገብ ዕውቀት    ገብይቶ
አገር እንዲያሳድግ    ኮትኩቶ::

የግፈኛው    ሞግዚቶች
በበሉበት    ጩሂዎች
የዘር ሥርዬት    መሥራቾች
ስግብግቦች
ለአገር ልዕልና    መሰዋትን
ሥር-ነቀል ለውጥ    ማምጣትን
ተፃርሮ የቆመ    ወልማጣ
አገር ጠፍታ ፍትሕ    ዘግጣ
ገዳያችን ተሸክሞ    እያምታታ

እኔ ልምራ ብሎ    ዞሮ መጣ::
ሥነ-ምግባራቸው    ውድመት!
ተልዕኮአቸው    ክህደት!
ዲያቢሎሳዊ    ቅናት! ቅጥፈት
የሠራውን    ግዙፍ ስህተት
የማያምን    ግብዝ ፍጥረት
ገፍታሪ ወደገደል    ወደ ፅልመት::

መብት ገፋፊ    የመኖር መብት
ያልተላበሰ    ሰባዊነት
ፈጣሪ የሰጠንን    ነፃ አንደበት
ቅርቅር! ክርትም    አርጎ ዘግቶ
ብልህ መሪ እንዳይወጣ    ጥፋት በዝቶ
ገደበ! አገደ!    ጊዜ/ቦታን ነስቶ::
ለካስ
ጊዜና ቦታ ሳይኖር    ሃቅ አትኖር
እንዴት ሆኖ?    ከየት መጥታ?
እስኪመቻች    እስኪጋጠም ሁኔታ
ትርቃለች ከኅሊና    ተለያይታ
በምትኳ ትኖራለች
ድንቁርና    ተንሰራፍታ::

አዲስ ማለት    ቀዳሚውን ተክቶ
ሲለወጥ ነው    ተያይዞ ነቅቶ! በቅቶ!
ባዲስ ራዕይ    ተነቃንቆ ተደራጅቶ
በጥበብ ላይ    ተመስርቶ::
ሆኖም
የሰው ልጅ ኅሊናው    እንዳይለወጥ
ተለውጦም    እንዳይመጥቅ
ባልፈቀደው!    ባልፈለገው!
እንዲያተኩር    ታቅዶ
የዘር መድሎን    ተለማምዶ

ታግቶ!　　　　　　ዘብጥያ ወርዶ
ተቀፍደዶ:- መንፈሱን　አላሸቀው
አቅመ-ቢስነት　　　እንዲሰማው
በሲያል ክበብ ውስጥ　አስገብተው
እንዲንፏቀቅ　　　　አድርገው
የፈጠረው　　　　　እስኪወስደው
መኖር እንኳን　　　እያቃተው
ድፍት ብሎ ይፀልያል　እንዲያላቀው::

5 ቢሊዮን　　　　　ዓመታት?
እግዚኦ!　　　　　የኛ ሲቃ
ገና ሳትደርስ　　　ያች ደቂቃ
ወዮ! ገና! ገና!
ከፊታችን　　　　　የተጋረጠው ጥበቃ
ሰቆቃችን　　　　　ላያበቃ
አንገታችን　　　　የሚያስደፋ
ደረታችን　　　　　የሚያስደቃ
መሆኑማ ታይቷል!　ታውቋል!
መገላገል ብቻ　　　ቀርቷል::

ባዙሪቱ ማዕከል　　ገብቶ ከመዋዠቅ
ከመላሸቅ
ይልቅስ　　　　　　ተነቃነቅ!
ከጉድጓዱ　　　　　እንድትርቅ
ማን? ለማን? ለምን?　የት? መቸ? እንዴት?
የሚለውን በምርምር　ዕወቅ! ጠይቅ!
እፎይ በል!　　　　ተንፍስ!
አቅመ-ቢስነት　　　ይብቃ!
አቅም ገንባ　　　　ተነቃቃ!
ድምፅ አሰምተህ　　እርታ!
የሞትን ታናሽ ወንድም ያን ዝምታ!
ለሕዝባችን ክብር　　ሁን መከታ!

ታገል! በርታ!

ሆኖም:-
ከዚያ ሳንደርስ ገና ከወዲሁ ሳንነቃ
አጣደፈን የእኛ አለቃ
አነጣጥሎ እያስመቸ ለስንጠቃ
እየገረፈ
በእሳተ ነበልባል እያንቃቃ
ፀጥ! እልም! ጭልጥ!
ብለን እንድናበቃ!
ታዘዘ!
በዓለም ፍፃሜ ዓለቃ::

የኢትዮጵያን ልጆች ተስፋ
አመንምኖ እንደልቡ ሊንሰራፋ
ልዩነት እንደግብ ታቅፎ እየተስፋፋ
ከልኩ አልፎ በተቋም እየተገፋ
ማቆሚያ በሌለው ቅጣት አገር እየለፋ
እንድትጠፋ
ብናኝ ሆና በጣም ደቃ!
ተለቃልቃ!
እንድታበቃ!

5 ቢሊዮን?
ይህ ሓቅ መሆኑን ተረድቶ
ሁኔታው እጅግ በጣም ተለዋውጦ
ያኔ!
ምን እንመስል ይሆን ከቶ?
የማይቀር ነገር ቢኖር-- "ትግል!"
የማይወገድ
ቢኖር ባይኖር ፈላጊ
ሁለንተናዊ ሕግ!

የዓለም ገዢ!    ድል አድራጊ!

በኃያሏ ተፈጥሮ    ተፈቅዶ
በመዋሃድና በመበተን    ተለያይቶ
ብተናን!
በዋናነት የያዘው    ተመራርጦ
ተዋውጦ!
ፍቅርን!
በጥላቻ ለማንበርከክ    ተነሳስቶ
በምትኩ እንዲሚላ    የግል ፍላጎቱ
ጎህ ቀዳጆችን    እየመቱ
ሰርጎ-ገብ ልከው    እያምታቱ
ያገር ንብረት    እየመጠጡ
የፍዳ ዘመናትን    አስጨለጡ::

ጥበብ እንዳይሰርፅ    ፈንጥቆ ብርሐኑ
እንዳይለካ    እንዳይዋሃድ ወጋገኑ
እንዲከስም    ማብራራቱ
እንዳይሰማ    መልዕክቱ
ጨለማ እንዲሆን    ማዕልቱ
ዝንተ-ዕለቱ
ፍሉይ! እንዳይሆን!    ከሌሊቱ::

የእምቢታ ቀን    ሳይደርስ ጊዜው
ተሎ ሊያጠናቅቁን    ዓልመው
ተነሳስተው
ዕቅዱ:- ስልቱ    ምቱ:- ዛቻው
አይገርምም    በማስተዋል ካየነ
ቁሳካላዊ ነፀብራቅ    ስለሆነ::

አወቅንብህ    አገር ገዳይ
የቁርጥ ቀን    ውልምጥ ባይ

ጠቋሚ ነህ    ቃል አቀባይ
አትታመን    ወዳጅ መሳይ
ጠምዛዛ የዞረብህ    ብልሃቱ
ምንስ ቢሆን    ላይቀር ሞቱ
ጀግኖቹማ
እምቢ! አሻፈረኝ!    ያሉ
ታግለው እያታገሉ    ይሰዋሉ
አደርጅተው
ሕይወት እንዲሆን    ቃሉ::

የመጀመሪያው    የሰው ፍጡሮች
የድንቅነሺ/ሉሲ    ዝርያዎች
በዝተው ተባዝተው    ዓለምን ሞልተው
ዕውቀት ያነሳቸው    ድንገት ስተው
አገርን በፍላፃ    መትተው
በድንቁርና
የተፈጥሮ ሕግጋትን    እየጣሱ
ያዳምን ልጅ    አስለቀሱ::

በያይነቱ ተበራክቶ    ሻጭ/ገዢዎች
ገበያው ደርቶ    የፍላፃዎች
ወደ ጉድጓዱ    ገፍታሪዎች
ቀባሪዎች!
ከተወሰነ "ሬድየስ"    አድርሰውን
በግፍተራ
እየተጥመለመልን    እንደ ሳይን/ኮሳይን
እንደነቡላ!
የእርሱማ ፍላጎቱ    የሚያሰላው እያደባ
በነበልባሉ እየነደድን    እንድንገባ
ወደ አዘቅቱ    ወደ አዛባ::

ባስገራሚ ፍጥነት    እንድንጠፋ

ፀንቶ በዕቅዱ      እየገፋ
ውድመትን      እንደዓላማ እያስፋፋ
እንግዴህ እንለበም!      አናንቀላፋ!
ልብ ያላችሁ      ብሩህ ተስፋ
ተነሱ! ቀስቅሱ!
ወግኑ!      እንዳንጠፋ!

ተወርዋሪው ኮከብ      እጅግ ግዙፍ
ከመሬት ቢላተም      በሃይል ሲከንፍ
በዚህም ምትሃት
ቢፈነዳስ የታመቀው      ባይቆለፍ
ወይም
በረዶ ቢጥል      ለዓመታት ሳያባራ
ሙቀቱስ ኃያል ቢሆን      አራራ!
የኛው ውጤት ነው      የኛው ሥራ::
የኑክ ጦርነትን      ቢጀምሩ
የሰውን ልጅ      ሊያሳርሩ
ያ! ስግብግቡ      እልክ ይዞት ግብዙ
ካልደረሰ      የልቡ
አፈንድቶ      ይላል ዝም
ተያይዘን      ስንወድም::

ስንጣጣር      ልናወጣ መሪ
ዘመናዊ ጥበበኛ
ማሰብ ስንጀምር      እኛ ለእኛ
መች ይኖራል      ግፈኛ?
በጋራ ስናጠፋው      ያን ምቀኛ
የሕዝብን ጠላት      ወደረኛ
ዓለም ትሆን ነበር      ደስተኛ::
ተመልሶ ለመምጣት      ቢከጅል ለሦስተኛ
ግን አይዞን!      ተመክሮ አለች ከኛ::

የቁም በድን ሳይሞት ሞቶ
ራዕዩ ሆዱ ብርሃን አጥቶ
በጨለማ ጉዞ ተስገብግቦ
እነሆ! ሆዱ ፈጥሮት
ሆዱ አርቆት ሆዱ አቅርቦት
ከጥቁሩ ጉድጓድ አስጠግቶት
እርሱን ያዩ
እርሱን መሳይ ተግተልትሎ
ግር! ብሎ ነጎደ! ተከታትሎ::

የተራራው እግርጌ እሥር ቤትማ
ዙሪያ ገቡ ገደላማ
ያሉት ክፍሎች በርካታማ
ጥልቅ ዋሻ ነው
የተዋጠ በድቅድቅ ጨለማ::
ለዓመታት ቆፍሮ ባዘጋጀው
የሰባዊነት ታጋዩን አሳደው
እግር ከወርቾ
በካቴና ጥፍር አርገው አሥረው!
እርስ በርስ አቆራኝተው
ቡድን በቡድን ለንፅሕና ወጥተው
ኳ! ኳ! ኪው! ቅልጪው!
ብረት ለብረት ሲጋጭ ሲፋጭ
ደፍ ሃ! ኡኡ!!
የሚል የሲቃ ድምፅ አየሩን ሲሰነጥቅ
ዓይናቸው ተሸፍኖ በዕራፊ ጨርቅ
መብራት አጥተው
ፀሐይ እንዳያዩ ተከልክለው
ሲገረፉ:- ሲረሸኑ የቀሩትን አሰምተው
አዕምሮን አሸብረው
ያጠፉታል አማቅቀው::

ፀገወይን:- ይስሓቅና በርጌ
ሰምጠው የቀሩበት
አበራሽ:- አምሃና ስጦታው
ደብዛቸው የጠፉበት
በለጠ:- ዮሴፍና ተክላይ
እነቱሉ የተዋጡበት
አበራ የማነአብን ከወገኑ የለዩበት
ቤተሰቡን አንገት ያስደፉበት
ፕሮፌሰር አሥራት አሰፋ ማሩ
ለሞት የበቁበት
ብርቱካንና ቤተሰቧ ያነቡበት
ዕልፍ አዕላፍ ዜጎች ግፍን የቀመሱበት
ገሃነም እሳትን በምድር ላይ ያዩበት
ተሰቃይተው ያለፉበት
ይህ ነው! አገር ጎታች ወደ ውድመት
ወደ አዘቅት! ወደ ፅልመት!

ግን:- ዕድሜ ለጊዜ! ለስዓቱ!
ለሲያል የዳረገን ገልቱ!
አሽከቱ! ዝተቱ!
በማጨብጨብ ያበረቱ
እየጠቆሙ ወገንን የሚያስመቱ
ወዳጆቹንም እንደማይምር ስላወቁ
ፈትለክ ፈትለክ እያሉ ለቀቁ
ይኸው ፍንትው ብሎ ወጣ ሃቁ!
ያ! እንጦርጦስ ጨለማው! ድቅድቁ!

አስተምረናል! ፅፈናል!
አሳይተናል! ነግረናል!
ሳንታክት በየጊዜው መክረናል::
የማይሰማ ባንዳ ከነመሪው ጣዖቱ
ብሻው ይግባ ከጉድጓዱ ቤቱ

ምን ጨነቀን ለእርሱ ዓይነቱ
የፈጠራቸውን ጋኔል ተሸክመው ቢዘምቱ
እልል ቢሉ ከበሮ እየመቱ
ጫካችንን መንጥረው ቢያጠፉ
ሰብል ማዕድናችንን ቢዘርፉ
ሕዝባችንን ቢገድሉ ቢጠየፉ
በሙሴ ጊዜ እንደሆነው
መደምሰሳቸውማ የማይቀር ነው::
ብቻ አስቡ ገራ-ገሩን አሳስተው
እንዳይሞቱ ተያይዘው::

ሥር- ነቀል ለውጥን ከተመኘህ
ክልብ አዝነህ ቁርጠኝነት ከተሰማህ
ፅልመቱ ካልናፈቀህ
ታዲያ ማን ይጣለው? የትኛው ዘር?
የማን አገር? ከኛ በቀር?
እናንት ፅልመትን የምትጠሉ
እንያያዝ! እንደጋገፍ! እስቲ በሉ::
ብርሃን እንዲፈነጥቅ ስለእኛ ለሚሞቱ
ዕውን እንዲሆን ምጥቀቱ!
እንዲዳብር ጉልበቱ!
መጀመር! መቀጠል! መጨረስና
ሆኖ መገኘት በትግል ሚና
ካልሆነማ አይገኝም በልመና::
አንድ ሆነን ስንዘምት አገር ልናቀና
አቅፈን የዘመናችን ድንቅ ፍልስፍና
ጥበብ ለጋሽ የዕውቀት ፋና
ሰብዓዊነት ነውና!!